DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የክልሉ የትምህርት ሹም ቢሮ

ፀደይ 2017

ይድረስ ለወላጆች/አሳዳጊዎች

በ2016-2017 የትምህርት ዓመት የፀደይ ወራት ላይ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የክልሉ የትምህርት ሹም ቢሮ (ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ.) በዲ.ሲ. ከሚገኙ የህዝብና የመንግስት ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (Youth Risk Behavior Survey (YRBS)) የተባለ ጥናት ያካሂዳል፡፡ የእርስዎ ልጅ ጥናቱን እንዳይሞላ ከፈለጉ የዚህ ደብዳቤ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን በመሙላት ለትምህርት ቤቱ ይመልሱ፡፡

ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ(YRBS)በወጣቶችና ጎልማሶች ላይ የሚታዩትን ለሞት፤ ለበሽታ፣ እንዲሁም ለተለያዩ የህብረተሰብ ችግሮች መንስዔ የሆኑ የጤና አደጋ ባህርያትን ለመቆጣጠር የተቀረፀ አሰራር ነው፡፡ እነዚህ የጤና አደጋ ባህርያት በቀደምትነት እንደ ያልታሰቡ ጉዳቶችና ሁከቶች፣ ወሲባዊ ባህርያት፣ የአልኮል መጠጥ እና የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ የትምባሆ ተጠቃሚነት፣ ጤናማ ያልሆነ የአመጋገብ ስርዓት፣ እና በቂ ያልሆነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ያጠቃልላሉ፡፡ የመረጃ ስብሰባው ጤናማ ያልሆነ ውፍረትንና አስምን የመሰሉ የጤና ውጤቶችን በተጨማሪ ያጠቃልላል፡፡ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ወሳኝ የጤና ሁኔታን እና መሻሻልን ጨምሮ በወጣቶች ወሲባዊ ባህሪ ላይ ብሄራዊ ብሎም አገር አቀፋዊ ትኩረት እንዲሰጥ ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) ይፈቅዳል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መረጃ ከፈለጉ በ http://www.cdc.gov/HealthyYouth/yrbs/index.htmላይ ስለሚገኝ ማየት ይችላሉ፡፡

ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) የተዘጋጀው በመጠይቅ ይዞታና አቀራረብ ሲሆን በመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ልጆች በአንድ የ 45 ደቂቃ የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ጥናቱ ስም የሚጠይቅ ስላልሆነ ተማሪዎች በነፃነት ጥያቄዎቹን በጥሩ ሁኔታ መመለስ የሚችሉ ይሆናል፡፡ ጥናቱ በፈቃደኝነት የሚደረግ ስለሆነ ተማሪዎቹ ጥናቱን አልጨረሳችሁም ተብለው ቅጣት አይቀበሉም፡፡ ሆኖም ግን ጥናቱ እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ የተማሪዎች ተሳትፎ በጣም ይበረታታል፡፡

**የእርስዎ ልጅ ጥናቱን ለመሙላት ከፈቀደ ተጨማሪ ስራ አያስፈልግም፡፡**የእርስዎ ልጅ ጥናቱን እንዳይሞላ ከፈለጉ ከስር ያለውን ክፍል ሞልተው፣ ፈርመውበት፣ ለልጅዎት ትምህርት ቤት ዋና ቢሮ ከ ሶስት የስራ ቀናት በፊት ይመልሱ፡፡ ምንም ዓይነት ጥያቄ ቢኖሮት እባክዎ የልጅዎትን አስተማሪዎች ወይም ርዕሰ-መምህር ይጠይቁ፡፡ በተጨማሪም ወ/ሮ Aimee Mclaughlin202-741-6481 ወይም በኢሜልOSSE.schoolhealth@dc.govማግኘት ይችላሉ፡፡

ከትህትና ጋር፣

ዶና አንቶኒ
ምክትል የክልሉ የትምህርት ሹም

**የተማሪ ስም:** ______________________________

ትምህርት ቤት: ______________________ ክፍል: ______________

ፎርሙን አንብቤዋለሁ ጥናቱም ስለምን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡

**[ ] አይ፣ ልጄ ይሄን ጥናት አይሙላ፡፡**

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ: ______________________ ቀን: ______________

## ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) ተፈላጊ መረጃ

ጥ. **ጥናቱ የሚከናወነው ለምንድነው?**

መ. ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) በወጣቶችና ጎልማሶች ላይ የሚታዩትን ለሞት፤ ለበሽታ፣ እንዲሁም ለተለያዩ የህብረተሰብ ችግሮች መንስዔ የሆኑ የጤና አደጋ ባህርያትን ለመቆጣጠር የተቀረፀ አሰራር ነው፡፡ እነዚህ የጤና አደጋ ባህርያት በቀደምትነት እንደ ያልታሰቡ ጉዳቶችና ሁከቶች፣ ወሲባዊ ባህርያት፣ የአልኮል መጠጥ እና የአደገኛ ዕፅ ተጠቃሚነት፣ የትምባሆ ተጠቃሚነት፣ ጤናማ ያልሆነ የአመጋገብ ስርዓት፣ እና በቂ ያልሆነ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ያጠቃልላሉ፡፡ የመረጃ ስብሰባው ጤናማ ያልሆነ ውፍረትንና አስምን የመሰሉ የጤና ውጤቶችን በተጨማሪ ያጠቃልላል፡፡ መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ወሳኝ የጤና ሁኔታን እና መሻሻልን ጨምሮ በወጣቶች ወሲባዊ ባህሪ ላይ ብሄራዊ ብሎም አገር አቀፋዊ ትኩረት እንዲሰጥ ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) ይፈቅዳል፡፡

ጥ. **ከጤና ጋር የተገናኙ ስሜት የሚነኩ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ?**

መ. አዎ፡፡ አንዳንዶቹ ጥያቄዎች ስሜት የሚነኩ ናቸው፤ ሆኖም ግን መልሶቹ ላይ ስም አይጠቀስም፡፡ ከመጠን ያለፈ ውፍረት፣ የአመጋገብ ስርዓት ችግር፣ የአእምሮ ህመም፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ እንዲሁም ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ዋና የጤና ችግሮች ናቸው፡፡ ወሲባዊ ግንኙነት እና በደም ስር የሚወሰድ አደገኛ ዕፅ አጠቃቀም የኤች አይ ቪና የአባላዘር በሽታዎች መሰራጨትን የሚጨምሩ ጎጂ ባህርያት ናቸው፡፡ ወጣቶች እዚህ አደጋ ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ብቸኛው መንገድ ስለነዚህ ባህርያት ጥያቄ በመጠየቅ ነው፡፡ እራስን የመግደል ሙከራ፣ የትምባሆ አጠቃቀም፣ አልኮል መጠጥና አደገኛ ዕፅ አጠቃቀም፣እንዲሁም መሣሪያ መያዝ ልብን የሚነኩ ርዕሶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎቹ በቀጥተኛ መንገድ ግን ልብን በሚነካ መልኩ የተፃፉ ናቸው፡፡

ጥ. **የተማሪዎቹ ስም ከጥናቱ ጋር ይያያዛል?**

መ. በጭራሽ፡፡ ጥናቱ ስም የማይጠይቅ ነው፡፡ ጥናቱ የልጅዎትን ሚስጥር ለመጠበቅ ተብሎ የተቀረፀ ነው፡፡ ጥናቱ በሚደረግበት ጊዜ ምንም ዓይነት ስም ወይም ማንነትን የሚገልፅ የትኛውም ዓይነት መረጃ አይወሰድም፡፡

ጥ. **ተማሪዎቹ ባህርያቸው መቀየሩን ለማወቅ ጥናቱን ከአንድ ጊዜ በላይ መውሰድ ይችላሉ?**

መ. አይችሉም፡፡ የተማሪዎቹ ማንነት በጥናቱ ውስጥ ስለማይካተት፣ የጤና ባህርያቸው መቀየሩን ለመመዘን አይቻልም፡፡

ጥ. **ልጄ በጥናቱ ውስጥ እንዲካተት እንዴት ተመረጠ?**

መ. የእርስዎ ልጅ ሊመረጥ የቻለው አሁን ባለበት/ባለችበት የክፍል ደረጃ አማካኝነት ነው፡፡ ጥናቱ በዲ.ሲ በሚገኙ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚደረግ ይሆናል፡፡

ጥ. **ጥናቱን ለመሙላት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

መ. ጥናቱ በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ያልቃል ተብሎ ይታሰባል፡፡(ወደ 45 ደቂቃ አካባቢ)

ጥ. **ተማሪዬ የሚጠየቃቸውን ጥያቄዎች እኔ ማየት እችላለሁ?**

መ. አዎ፣ የጥናቱን ኮፒ ጃንዋሪ 2017 ላይ ከልጅዎት ትምህርት ቤት ማግኘት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ያለፉ ጥናቶችን ከ http://osse.dc.gov/service/youth-risk-behavior-surveyላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ጥ. **በተጠቀሱት ርዕሶች ላይ እኔና ልጄ ወጣቶችን በተመለከተ ይበልጥ ለመማርና ለማወቅ ብንፈልግስ?**

መ. ጥናቱን ከወሰደ በኃላ በጥናቱ ላይ የተሳተፈ ተማሪ በጠቅላላ፤ ለወጣቶችም ሆነ ለሚያሳድጓቸው መረጃና እርዳታ ሊሰጡ የሚችሉ የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ የከተማ ወኪሎች፣ እና ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ ድርጅቶችን የሚዘረዝር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ እርስዎም እንዲያገኙት የወረቀቱን ኮፒ የልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ማግኘት ይችላሉ፡፡

ጥ. **ከጥናቱ የሚገኘው መረጃ በምን መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል?**

መ. ከጥናቱ የሚገኘው መረጃ ፖሊሲ ለመቅረፅ እንዲሁም በብሄራዊና አገር አቀፋዊ ደረጃ ገንዘብ ለማዋል ተጠንቶ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡የ ዩዝ ሪስክ ቢሄቭየር ሰርቬይ (YRBS) ያለፉት ዓመታት የጥናት ውጤቶች በኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. ድህረ-ገፅ www.osse.dc.govላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ የሚገኘው መረጃ በብሄራዊ ደረጃ በበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል (Centers for Disease Control and Prevention) ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በ2017 መረጃው ሲለቀቅ በ www.cdc.gov/HealthyYouth/index.htmላይ ማየት ይቻላል፡፡